

ለምለም አንዳርጌ(ከኦስሎ) 07/07/2013

# ህልም አለኝ

እህህ አለች እማማ እህህ አለች ሃገሬ፣

ተብትቦ በያዛት በነከሳት አውሬ፡፡

ሴት እናት እህት ናት ሴት የሃገር እመቤት፣

የዘር ትብታብ ልቃቂት፣

የፍጡራን ሚስጥር እምብርት፣

ካስማ ማገር የአንድነት፡፡

ግና ዛሬ ውልሽ ጠፍቶ፣

ክብርሽ ዝናሽ ተቀምቶ፡፡

አሳር ግፍ ሲወርድብሽ፣

ቤት ማጀቱ ሲኀልብሽ፡፡

ተጥለሻል በየሃገሩ፣

ገረድ ልትሆኝ ለቱጃሩ፡፡

ሃገርንሽ እምነትሽን በዘረኞች ተቀምተሽ፣

ከንቱ ሆነሽ ያለ ቅሪት በሰው ሃገር ትኖሪያለሽ፡፡

ስደት ሆኖ ያንቺ እጣ፣

ሆነሽ ቀረሽ ከብሩን ያጣ፡፡

ግና ህልም አለኝ የእውነት፣

ሴት እናት ልትሆን ቃሏ የሚሰምርበት፡፡

ሲነሳ ምንሽር ሲወለወል አልቤን፣

ህዝባችን ሆ ሲል ሲቃረብ የድል ቀን፡፡

እናትም እህትም ሃገርም ነኝና፣

በቅርብ ይታየኛል የነጻነት ፋና፡፡

ህዝባችን ሃያል ነው ለድል መሰረት፣

ከፋፋይ ጉጅሌን የሚያስደፋ አንገት፡፡

ህልም አለኝ  ሃገሬ ቅርብ ነው ይነጋል፣

በህዝባችን ሃይል ጠላትሽ ይወድቃል፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ

ሞት ለወያኔ!!!

ለአስተያየቶ- Wueltaw@yahoo.no